# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ(ኢሕአፓ)
*Ethiopian People´s Revolutionry Party(EPRP*

## ሕዝብ ማፈናቀል የወያኔ ባህሪ ነው፤ ወያኔና ሕብረብሔራዊ ኢትዮጵያ፡ እሳትና ጭድ ናቸው!!

ሚያዚያ 2005 ዓ.ም.

የኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜትና በተለይም ደግሞ የሕብረ ብሔር ጠላት የሆነውን የወያኔን ምንነት በሚገባ የሚያውቀው ኢሕአፓ በቅርቡ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ከ 20 ዓመት በላይ የኖሩና ከክልሉ ተወላጆች ጋር ተጋብተው የተዋለዱ፡ ኃብትና ንብረት ያፈሩ በአማራ ብሔር ዜጎቻችን ላይ የደረሰውን በጥላቻ የተሞላ የማፈናቀል ድርጊት ክፉኛ ያሳዘነው፡ ልቡንም ያቆሰለውና አጥብቆም የሚያወግዘው እንደሆነ አበክሮ ይገልፃል። አዛውንት፡ ሕጻናትና ሴቶች፡ ከአራስ ያላገገሙ እናቶች ሳይቀሩ፡ ያፈሩትን ንብረትና የዘሩትን እህል ሳይሰብስቡ በጉልበት እንዲፈናቀሉ ተደርገው ለመጠለያ ቢስነት መዳረጋቸው ወያኔ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር የማጥፋት እቅዱ ቀጣይ ዘመቻ በመሆኑ ለጊዜው እንዲገታ ለማድረግ እንደ ሕዝብ ባለመቻላችን ያናድዳል፡ ያንገበግባል፡ ያስመርራልም።

በተመሳሳይ መልኩ በደቡብ ክልል ቤንች ማጂ ዞን ጉረፈርዳ እንዲሁ ለረጅም ዓመታት በመኖር ሃብትና ንብረት አፍርተው ተዋልደው የኖሩ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ላይ የማፈናቀል እርምጃ ተወስዶባቸዋል። ከአፋር፡ ከጅጅጋም በአማራው ብሄረሰብ ዓባላት ለዚሁ ጭፍን ጥላቻ ለተሞላበት የዘር ማፅዳት እርምጃ  ሰለባነት ተዳርገዋል። ለነዚህና በተለያዩ ጊዜና ቦታዎች በበደኖ፡ በአረካ፡ በአርባ ጉጉ በአማራ ብሔር ላይ ሆን ተብሎ ለተደረጉ አሰቃቂ ጭፍጨፋዎች  ዋና ተጠያቂ የሆነውን የወያኔ ቡድንና በጠባብነት የታወሩ ደጋፊዎችን በዚህ ከሰብአዊነት ውጭ በሆኑ ድርጊቶቻቸው በኢትዮጵያና በአማርኛ ተናጋሪ ዜጎቻችን ላይ ያላቸውን ጥላቻ ከምንጊዜውም በበለጠ የሚያሳይ ከመሆኑም ሌላ በተባበረ ሀገር ወዳድ ትግል እንዲገታ ካልተደረገ መጨረሻው ምን ሊመስል እንደሚችል ከበርካታ ተመክሮዎች አንፃር ሲሰላ  በእጅጉ የሚያሳዝንና የሚቀፍ በመሆኑ ሁሉም ልብ ሊለው የሚገባ ነው።

በርግጥም ሁኔታውን በጥሞና ለተመለከተና ወያኔዎች ለሚያደርጉት የማፈናቀል ድርጊቶች የሚሰጡትን መግለጫ ለሚያጤን እንዲሁም ወያኔ ራሱ የደነገገውን ሕግ ራሱ እንዳሻ የሚጥስና ለከፍተኛ ባለሥልጣናቱ የማይሰራ መሆኑ ከግምት ሲገባ የወያኔን ሕገ አገዛዝ አንቀጾችን እያጣቀሱ እሱኑ ለመሞገት መጣር ትርጉም የለሽ እንደሆነ ግልፅ ነው።  ግፍና በደል በሚያሰቅቅ ሁናቴ እንዲያርፍበት ለተደረገ ማንም ሰው በዚህም ተከላካይ የሚያጣ የድርጊቱ ሰለባ የሆነ ተበዳይ አርቆ አስተዋይነትና አሳቢነት ቦታ የሚሰጣቸው በጣም ኢሚንት በመሆኑ ሌላ የትግል አቅጣጫ ለመፈለገ እንደሚገደድ መገመት የሚያስቸግር አይደለም። ስለሆነም ይህ አስጊ የሆነ ሁኔታ ከመከሰቱ በፊት በኔ ላይ አልደረሰም በሚል በተሳሳተ አመለካከት ዝምታን መምረጥ ጨርሶ መወገድ ይኖርበታል። ሂደቱ ወዴት እንደሚሄድ ግልፅ ነውና። ስለዚህም በዘረኝነት ያልተለከፈ ማንም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊና ለሕዝባችን ቀናኢ የሆነ ሁሉ ይህንን የመሰለ አሰቃቂና አሳዛኝ ድርጊትን በዝምታ ሊመለከተው የሚገባ አይደለም።  ይህ ብቻ ሳይሆን ድርጊቱን ከማውገዝና መግለጫ ከማውጣት ባሻገር ለድርጊቱ መቆም መፍትሄው ወያኔንና ጠባቦች የሆኑ ደጋፊዎቹን ሕገ ወጥ በሆነ ሁኔታ ከያዙት ከሥልጣናቸው በቆራጥ ትግሉ ማስወገድ የውዴታ ግዴታ ነው በማለት አፅንዖት ሰጥተን ስሜታችንን የምንገልፀው ።



**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email [ESPIC@aol.com](mailto:ESPIC@aol.com)**
**Website [WWW.EPRP.com](http://WWW.EPRP.com)**

**EPRP**
**BP 22**
**92270 Bois Colombes**
**France**

**Tel. 202 291 4217  Fax: 202 291 7645**

*የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ(ኢሕአፓ)*

*Ethiopian People´s Revolutionry Party(EPRP*

የወያኔና የጠባብ ቡድኖች የጥላቻ ሰለባ የሆነው ኢሕአፓ ይህንን ድርጊት የሚያወግዘው ለሀገር ወዳዱም ጥሪ የሚያቀርበው ገና ከጥንስሡ ሁሉም ብሔረሰብ ተገነጣጥሎ በየራሱ ነፃ ሀገርና መንግሥት ያቋቁም የሚለውን አገር አፍራሽ ፖለቲካ ወያኔ ማራመድ ሲጀምር ሂደቱ ወዴት ሊወስድ እንደሚችል በመገንዘብ አጥብቆ በመቃወሙና ጠቃሚው በዴሞክራሲ መከበርና በእኩልነት ላይ ለምትመሰረት ለአንዲት ኢትዮጵያ መታገልን በመጠቆሙ ሲሆን ዛሬ ይህንን አስጻያፊ ድርጊት እየፈፀሙና እያስፈፀሙ ባሉ ጠባብ ቡድኖች በተለይም በወያኔና ሻዕቢያ በተደጋጋሚ በጦር እንዲጠቃ የተደረገው ያለ ምክንያት አለመሆኑን በሚገባ ስለሚያውቀው ነው። ይኸው ጥቃት ኢትዮጵያን በሚጠሉ ኃይሎች ስፍቶና ዳብሮ ለኢትዮጵያ ቆመናል የሚሉ ኃይሎችም ዝምታን መምረጥና የተቆርቋሪ ስሜት ባለማሳየታቸው ውጤቱ ይኸው በጠቅላላው ኢትዮጵያ ስልት በተሞላበት አኳኋን እየተደረገ ይገኛል። ወያኔ በባዕዳኖች ሙሉ ድጋፍ የጨበጠውን የፖለቲካ ሥልጣን በመጠቀምና በሚረግፍለትም የኤኮኖሚ እርዳታ ጠባብ ቡድኖችን በስሩ ለማሰለፍና መጠቀሚያ ለማደረግ መቻሉ ሕዝባችንን ለመናቅና ማን ይነካኛል የሚል እብሪት በውስጡ በማሳደር በጥላቻ የሚመለከታቸውንና ይቀናቀኑኛል የሚላቸውን የብሔረሰብ አባላት እየከፋፈለ የማፈናቀል እርምጃውንም እያካሄደ የከፋፍለህ ግዛ መርሁን ተግባራዊ እያደረገ እሳካሁን ቀጥሏል። ለዚህም ነው ይህንን በእብሪት የተወጠረ ማንአህሎኝነቱን ማስተንፈስና ሕዝባችንን መታደግ ቀነ ቀጠሮ ሊሰጠው አይገባም በማለት ኢሕአፓ ሳይታክት የሚቀሰቅሰው።

የወያኔ አገዛዝ በመላው ሀገሪቱ እየተባባሰ ለቀጠለው የሰብአዊ መብት ጥሰት ብቻ ሳይሆን ለመጀመሩም ዋና ተጠያቂ መሆኑ ለሁሉም ግልፅ ቢሆንም ለችግሩ ተመጣጣኝ በሆነ ስልት ካልተቋቋሙት እንዲሁ በከፋ ሁኔታ መቀጠሉ አይቀሬ ነው። የሚታየውም ይኸው ነው። ይህ ብቻ አይደለም። ለሥልጣን ከበቃ ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ አመቺ ጊዜና ሁኔታ እየጠበቀ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ወገኖቻችን ላይ በተለያዩ አካባቢዎች ለበርካታ አመታት ከሚኖሩበት አካባቢ በተደጋጋሚ የወሰዳቸው የማፈናቀል እርምጃዎች የሚታወቁ ናቸው። የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆነውን በተለይም የአማራውን ብሔረሰብ በጎጥ እየለየ ጎንደሬ፡ ጎጃሜ፡ የወሎ የሸዋ እያለ በመከፋፈል፡ በቤተክርስቲያን ጭምር በዲያስፖራው ሳይቀር እየከፋፈለ ለማዳከም እያደረጋቸው ያሉ ጥረቶች በቀጣይነት እየተካሄዱ ያሉ በገሃድም የሚታዩ ናቸው። ይህ እንዳለ ሆኖ የወያኔን የሕዝብ ጠላትነት በሚገባ ባለመገንዘብና ማንነቱን እያለዘቡ በማቅረብ የተደረጉት እንቅስቃሴዎችም ለወያኔ መጠናከርና የሕዝብን ስብአዊ መብቶችን ለመጣስ እንዲቻለው አስተዋፅዖ ማበርከቱም የሚዘነጋ ሊሆን አይችልም። በሂደት በምክርና ተመክሮ በማግኘት ይሻሻል ይሆናልና ጊዜ እንስጠው በማለት የሞከሩም የወያኔ አምባገነናዊ ድርጊትና ጥላቻ ሰለባ ከመሆን ሊያመልጡ አልተቻላቸውም። እነዚህ ሁሉ ትምህርት ሊሆኑን በተገባ ነበር። ግና አልሆነም።

በቅርቡ እየተደረጉ ያሉት የማፈናቀል እርምጃዎችና የወያኔ የጥላቻ ሰለባ በሆነው አማራ ብሔረሰብ ላይ ብቻ ያተኮረ ቢሆንም ሌሎችም ጽዋዉን ለመጎንጨት እየተገደዱ ናቸው። መጠነ ሰፊ ቁጥር ያላቸው ጋምቤላዎች፡ ቤንሻጉሎች፡ አሮሞዎችና ሌሎችም ለበርካታ ዓመታት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ለኑሮ ከሚጠቀሙበት መሬታቸው በግዴታ እየተፈናቀሉ መሬታቸው ለባዕዳን በተለይም ለሕንዶች፡ ለሳዑዲ አረቢያና ለተለያዩ የአረብ ሀገራት በርካሽ የተሸጠባቸው መሆኑ የዚሁ ሌላው አስከፊ ገፅታ ነው። ርዝመቱ ከሺ ኪሎሜትር በላይ የሆነና ወደ ውስጥ ደግሞ ከ50 እስከ 70 ኪሊሜትር ያለውን የኢትዮጵያ ግዛት ለሱዳን በተሰጠበት ወቅት በኃይል እንዲፈናቀሉ የተደረጉት የአርሶ አደሮች ጉዳይም እንደዚሁ የወያኔ ፖሊሲ ነፀብራቅ ነው። መፈናቀል ብቻ ሳይሆን ለሞትም የተዳረጉት ቁጥራቸው በርካታ ነው። በየእስር ቤቱ የታጎሩ በተለይም የኦሮሞ ዜጎቻችን ቁጥራቸው በብዙ ሺ የሚቆጠር ነው።



EPRP
P.O.BOX 73337
Washington DC, 20056
USA

Email ESPIC@aol.com
Website WWW.EPRP.com

EPRP
BP 22
92270 Bois Colombes
France

Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645

ከሁሉም በላይ በኔ አውቅልሃለሁ አባዜ የትግራይ ሕዝብ በፍላጎቱ ሳይወክለው ከሌሎች ወንድምና እህቶቹ ጋር በጋራ በአንድነት ሊኖሩ አይችሉም በማለት የትግራይ ሕዝብ እንዲገነጠል ያደረገውን የጥላቻ በተለይም በሸዋ አማራ ላይ ያካሄደውን ቅስቀሳ አደገኛነቱን አውቆ በመታገሉ የጦር ውጊያ ከፍቶበት በደም እንዲታቡ ማድረጉም የሚታወስ ነው። ይህ ብቻ አይደለም። ኢሕአፓ ለሰብአዊነት ያለው ራዕዩና ለዜጎቻችን ያለው ፍፁም ፍቅርና አክብሮት ይህንን የመሰለ ወራዳ ድርጊት አጥብቆ ለመኮነን ዋናው መሰረቱ በመሆኑ ጭምር ነው።

ይህ ጠባብና አረመኔ ቡድን ገና ሲፈጠር ፀረ - አማራነቱን ያለ ሀፍረት ይፋ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን የቅኝ ገዢዎች ኢትዮጵያን የመበታተን የቆየ እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የተተከለ መሆኑና አገር የማጥፋት ተግባሩ በጨመረ ቁጥር የሚፈስለት እርዳታም በዛው ልክ ማደጉ እንዲሁ በዘፈቀደ እንዳልሆነ ልብ ልንል ይገባል።

በመሆኑም የወያኔን ፀረ አማራነት በሱም ተመርኩዞ ኢትዮጵያን እንደሀገር ለማጥፋት እያደረገ ያለውን ድርጊት ለማስቆም የሚቻለው ወያኔ ፀረ ሕዝብ፡ ፀረ ኢትዮጵያ መሆኑን ተገንዝቦ በዚሁ ላይ የተመሰረተ የወያኔን ሥርአት ለማስወገድ በሚደረግ ፅኑ ትግል ብቻ ነው። እሱን በመኮረጅ ሳይሆን እሱን ተጻጻሪ ሆኖ በመቆም አጥብቆ በመታገል ነው። ይህ ስኬታማ ሲሆን ያኔ ኢትዮጵያ የሁላችን በማድረግ በሰላምና በእድገት ጎዳና ለመጓዝ ሁሉም በሚችለው አቅሙ የራሱን አስተዋፅዖ ሊያበረክት የሚችልበና እንደ አይን ብሌናችን በጋራ የምንንከባከበው መድረክ የሚኖረው። መሰረቱም በጋራ የሚገነባ ነውና ማንም ከቶ ማንም ኃይል ሊያፈራርሰው አይችልም።

የወያኔን የማፈናቀል እርምጃ ለማገድ እንታገል!!

በጋራ ትግል እናቸንፋለን!



**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email** **ESPIC@aol.com**
**Website** **WWW.EPRP.com**

**EPRP**
**BP 22**
**92270 Bois Colombes**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**